# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ

## የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ሥራዎች የማበረታቻ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 158/2016




ሚያዝያ/2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ሥራዎች የማበረታቻ

## የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 158/2016

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በከተማው የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በዓይነት እየተለየ በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል፤ ወደ ማስወገጃ ቦታ የሚጓጓዘውን የቆሻሻ መጠን ለመቀነስ እንዲሁም በቆሻሻ ምክንያት የሚከሰትን የአካባቢ ብክለት በመከላከል ጽዱና ውብ ከተማ ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ከደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት በማዘጋጀት እና የወረቀት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስበው የሚሸጡ በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፉ የተሰማሩ ማህበራትን ማበረታታት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም በከተማችን ውስጥ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ከ 65 እስከ 70 ፐርሰንት የሚሆነው የሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ እና የወረቀት ተረፈ ምህርት ደረቅ ቆሻሻ በመሆኑ ይህን ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ወደ ሀብት በመቀየር የከተማዋን ጽዳት ለመጠበቅ የማበረታቻ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

ስለዚህ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፤ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ሥራዎች የማበረታቻ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር** 158/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

### 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. ***"ኤጀንሲ"*** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
2. ***"ማህበር"*** ማለት የወረቀት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስበው ለመሸጥ በህጋዊ መንገድ የተደራጁ ወይም ከደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት አምርተው ለመሸጥ በህጋዊ መንገድ የተደራጀ ቡድን ነው፤

3. ***ኮምፖስት"*** ማለት ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ (ከቅጠላ ቅጠል፣ ከሳር፣ የምግብ ትርፍራፊ፣ የአትክልትእናፍራፍሬ ተረፈ ምርት) ውህደትን በማብላላት የሚመረት ነው

4. ***"ወረቀት"*** ማለት አገልግሎታቸውን የጨረሱ ካርቶኖች፣ ጋዜጦች፣ ክላሰሮች ፣የዕቃ መያዣ (ካኪፖስታዎች) ፣ የፅህፈት መሳሪያዎች (ደብተር ማስታወሻ)፣ የህትመት ውጤት ነው፣

5. ***"ማበረታቻ"*** ማለት ወረቀትን ሰብስቦ ለሚሸጥ ወይም ኮምፖስት አምርቶ ለሚሸጥ ማህበር በሸጠው የወረቀትና ኮምፖስት መጠን ኤጀንሲው በሚወስነው ታሪፍ መሰረት በኪሎግራም ወይም በሜትርኩብ እየተሰላ የመልሶ መጠቀምናኡደት ማድረግ ስራን ለማበረታታት ለማህበሩ የሚከፈል ክፍያ ነው

### 3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየወረዳው ወረቀት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስበው እና ኮምፖስት አምርተው በሚሸጡ ማህበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ማበረታቻ የሚሰጣቸው የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎችና ማህበራት

### 4. ማበረታቻ የሚሰጣቸው የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች

1. በከተማው ውስጥ ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ተሰብስቦና ተለይቶ በህጋዊ መንገድ የተሸጠ የወረቀት ደረቅ ቆሻሻ፣
2. በከተማው ውስጥ ከሚመነጨው የሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ (የአትክልትእናፍራፍሬ ፣ የምግብ ተረፈ ምርትን፣ ሳርና ቅጠላ ቅጠልን) በማብላላት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ተመረቶ በህጋዊ መንገድ የተሸጠ ኮምፖስት (ቀልዝ)፣

### 5. ማበረታቻ ስለሚደረግለት ማህበር

1. የወረቀት እና ኮምፖስት ድጎማ የሚከፈለው ማንኛውም ማህበር በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ በህጋዊ መንገድ የተደራጀና ከተደራጀበት

ወረዳ የንግድ ምዝገባ ፍቃድና ሰርተፍኬት፣ የግብር ከፋይነት ሰርተፍኬት እና የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ያለው ሊሆን ይገባዋል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ማህበር የወረዳው ጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት፣ የክፍለ ከተማው ጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና ኤጀንሲ እንዲያውቁትና እንዲመዘግቡት ካልተደረገ በስተቀር ማበረታቻው ሊከፈለው አይችልም፣

3. ለማበረታቻ ክፍያ በኤጀንሲ የተመዘገበ ማንኛውም ማህበር የማበረታቻ ክፍያ ማግኘት እንዲችል ኤጀንሲው ለስኬት ባንክ ደብዳቤ ሊጽፍለት ይገባል፣
4. ከመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ውጭ የተደራጀ ማንኛውም ማህበር ወይም ግለሰብ የኮምፖስትም ይሁን የወረቀት ማበረታቻ ክፍያ አይሰጠውም፣

5. የወረቀት ቆሻሻ ማበረታቻ (ድጎማ) ክፍያ የሚሰጠው ማህበሩ ከምንጩ ወረቀትን ለሚሰበስቡ ወይም ከማህበራት ግዥ ለማይፈጽሙ ሲሆን እና የማበረታቻ ድጎማ መጠን በወር 50,000 ሺ (ሃምሳ ሺ) መብለጥ የለበትም።

6. ስለ ስራ ውል ስምምነት

1. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ዘርፍ የተደራጀ ማህበር የወረቀት እና የኮምፖስት ማበረታቻ ለማግኘት የተደራጀበትን ህጋዊ ሰነድ በማያያዝ ከወረዳው የጽዳት ጽህፈት ቤት ጋር የስራ ውል ስምምነት ሊኖረው ይገባል፣

2. ማንኛውም በወረቀት መሰብሰብ የተደራጀ ማህበር የማበረታቻ ክፍያ የሚከፈለው ንግድ ፈቃዱን ካወጣ ቀን ጀምሮ በሚታሰብ ለሁለት ዓመት ብቻ ነው፣

3. ማንኛውም ለኮምፖስት ማምረት የተደራጀ ማህበር ማበረታቻ ክፍያ የሚከፈለው ንግድ ፈቃዱን ካወጣ ቀን ጀምሮ በሚታሰብ ለአምስት ዓመት ብቻ ነው፣

4. ማንኛውም የወረቀት ወይም የኮምፖስት ማበረታቻ ተጠቃሚ የነበረ ማህበር በተለያየ ምክንያት ቢፈርስና ከማህበሩ አባላት መካከል ከ50 ፐርሰንት በላይ የሚሆኑት በአዲስ መልክ በጋራ ሆነው በሌላ ማህበር ስም ቢደራጁ የማበረታቻ ክፍያ አይሰጠም፣

## ክፍል ሶስት

## ስለ ማበረታቻ አቀራረብና አወሳሰን

### 7. የወረቀት እና ኮምፖስት ማበረታቻ ለመጠየቅ የሚያስፈልግ መረጃ

1. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ተደራጅቶ ከወረዳው ጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ጋር ህጋዊ ውል የተዋዋለ ማህበር የወረቀት ወይም የኮምፖስት ማበረታቻ ሲጠይቅ በህጋዊ የማህበሩ ማህተም ወጭ የተደረገ ደብዳቤ ምን ያክል ግብዓት እንደሸጠ በኪሎ ግራም ገልጾ ጥያቄውን ለወረዳው ጽዳት አስተዳር ጽህፈት ቤት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ የተደራጀ ማህበር የወረቀት እና የኮምፖስት ማበረታቻ ለወረዳው ጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት በደብዳቤ ሲጠይቅ ግብዓቱን የሸጠበትን በገቢዎች የተመዘገ የማህበሩ የሽያጭ ደረሰኝ ኦርጅናል አያይዞ የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የወረቀት እና የኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ የሚጠይቅ ማህበር የራሱን ኦርጅናል የሽያጭ ደረሰኝ እና ግዥውን የፈጸመለት ተቋም፣ ድርጅት ወይም ማህበር ግዥ ለመፈጸሙ የሚገልጽ ከተቋሙ፣ ከድርጅቱ ወይም ከማህበሩ በህጋዊ ቁጥርና ማህተም የተጻፈ ደብዳቤ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

4. ኮምፖስት በከተማ ግብርና ለተሰማሩ ግለሰቦች የሚሸጥ ማንኛውም ማህበር ሽያጭ ለማከናወኑ ህጋዊ ደብዳቤ ማቅረብ የማይችሉ በመሆናቸው በወረዳው የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ የኮምፖስት ግብይቱ ስለመከናወኑ መጠኑን በኪሎ ግራም ጠቅሶ በህጋዊ ደብዳቤ ካረጋገጠ የማበረታቻ ክፍያውን በደረሰኙ መሰረት መክፈል ይቻላል፡

5. የወረዳው ጽዳት አስተዳር ጽህፈት ቤት ማህበሩ የጠየቀውን የወረቀት እና ኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ የሽያጭ ሰነዶችን በተገቢው ሁኔታ በማጣራትና በማረጋገጥ በወረዳው የጽዳት ጽህፈት ቤት ኃላፊ በሚጻፍ በደብዳቤ ለክፍለ ከተማው ጽዳት አስተዳር ጽህፈት ቤት ክፍያ ያሳውቃል፤

6. ኮምፖስት ከደረቅ ቆሻሻ በተገቢው ሁኔታ ሳያመርቱ የእንስሳት እበት ወይም ፍግ (እዳሪ) እና አፈር ብቻ ሰብስበው ለሚሸጡ ማህበራት የኮምፖስት ማበረታቻ ድጎማ አይከፈልም፡፡

8. **የወረቀት እና የኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ አሰጣጥና መጠን**

1. የክፍለ ከተማው ጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ከወረዳ የመጣለትን የወረቀት እና ኮምፖስት ማበረታቻ የክፍያ ሰነድ በማጣራትና በማረጋገጥ ክፍያ እንዲፈጸም በክፍለ ከተማው ጽዳት አስተዳደር ጽህፈት ቤት ኃላፊ ፊርማ ለጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ክፍያ እንዲያዝ ያሳውቃል፤

2. የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ከክፍለከተማ የመጣለትን የወረቀት እና ኮምፖስት ማበረታቻ የክፍያ ሰነድ በማጣራትና በማረጋገጥ ክፍያ እንዲፈጸም በጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወይም በምክትል ዋና ዳይሬክተር ኃላፊ ፊርማና ቲተር ለስኬት ባንክ በደብዳቤ ክፍያው እንዲከፈል ያዝዛል፤

3. የኮምፖስት፤ የወረቀት ማበረታቻ ክፍያ የሚፈጸመው በስኬት ባንክ በኩል ነው፤

4. የወረቀት እና ኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ካልተፈጠሩ በስተቀር በየወሩ መጨረሻ ከቀን 25-30 ባሉት ቀናት ተጣርቶና ተረጋግጦ ለማህበሩ ክፍያ ይፈጸማል፤

5. አሁን ባለው ዋጋ ለአንድ ኪሎ ግራም ኮምፖስት ማበረታቻ ብር 3.00 (ሶስት ብር) ወይም አንድ ሜትር ኩብ ኮምፖስት ማበረታቻ ብር 800.00 (ስምንት መቶ ብር) እንዲሁም አንድ ኪሎ ግራም ወረቀት ማበረታቻ ብር 1.50 (አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ይከፈላል፤

6. ኤጀንሲው ለኮምፖስት፤ ወረቀት ማበረታቻ ክፍያ እንደ ሁኔታው ዋጋውን ከፋይናንስ ቢሮ ጋር በመነጋገር ሊያሻሽል፤ ሊያቆም ወይም ሊያራዝም ይችላል፤

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**9.የማበረታቻ ክፍያ ስለማቋረጥ**

1. ማንኛውም የማበረታቻ ክፍያ የተፈቀደለት የኮምፖስና የወረቀት ማህበር የአሰራር ችግር ታይቶበት በኤጀንሲው የቃል እና የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ ከተወሰደበትና ችግሩን በ2 (ሁለት) ወር ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ የማበረታቻው ክፍያ ተጠቃሚነት ይቋረጣል፡፡
2. ኤጀንሲው የማበረታቻው ክፍያ አያስፈልግም ብሎ ሲያምን የማበረታቻ ክፍያን ማቋረጥ ይችላል፡፡

**10. የመተባበር ግዴታ**

❖ ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማስፈፀም ረገድ በዚህ መመሪያ ከተጠቀሱት አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**11. መመሪያውን ስለማሻሻል**

❖ ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

**12. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

❖ ከዚህ መመሪያ ውጭ ያሉ መመሪያዎችና የውስጥ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**13. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

❖ ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሚያዝያ/2016

እሸቱ ለማ (ፒ.ኤች. ዲ)

ዋና ዳይሬክተር

የአዲስ አበባ ከተማ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ